# ትምህርት 42

1. እግዚአብሔር አዳኝ እልካለሁ ካለ ብዙ ዓመታት ስላለፉ፥ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ረስቶአል ማለት ነው?

ሀ- አይደለም።

2. እግዚአብሔር ስለሚመጣው አዳኝ መልእክቱን ያስተላለፈው ለማን ነበር?

ሀ- ለነቢያት።

3. ስለ አዳኙ መምጣት እግዚአብሔር ለነቢያት የተናገረው መልእክት የሚገኘው የት ነው?

ሀ- በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ።

4. አብዛኛዎቹ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ነቢያት የተናገሩትን መልእክት ሰምተዋል?

ሀ- አልሰሙም።

5. እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ነቢያት ላይ ምን አደረጉባቸው?

ሀ- ገደሏቸው።

6. የእግዚአብሔርን ነቢያት ከመስማት ይልቅ እስራኤላውያን ማንን ሰሙ?

ሀ- ሐሰተኞቹን ነቢያት።

7. ሐሰተኞቹ ነቢያት እነርሱ የእግዚአብሔርን እውነት እንደሚናገሩ ገለጹ የተናገሩት ግን ምን ነበር?

ሀ- የሰይጣንን ውሸት።

8. እስራኤላውያን የቀረጿቸውን ምስሎች እያመለኩ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለእርሱ ያቀርቡ የነበረውን አምልኮ እግዚአብሔር ተቀብሏል?

ሀ- አልተቀበለም።

9. እስራኤላውያን የቀረጿቸውን ምስሎች እያመለኩ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለእርሱ ያቀርቡ የነበረውን አምልኮ እግዚአብሔር ያልተቀበለው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም አምልኮአቸው የከንፈር እንጂ ከልብ ያለመሆኑን እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው።

ለ- ምክንያቱም የተቀረጹ ምስሎችን ከልብ እንደሚያመልኩ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው።

10. ስለልባችን ሁሉን ነገር የሚያውቅ ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር።

11. እግዚአብሔር ስለ ልባችን ምን ይላል?

ሀ- እግዚአብሔር ልባችን ሁሉ በኃጢአት መሞላቱን ይናገራል።

12. ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ እስራኤላውያን ለተቀረጹ ምስሎች ቢሰግዱም እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመልኩ እስራኤላውያን ነበሩ?

ሀ- አዎን ጥቂቶች ነበሩ።

13. እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመልኩት እስራኤላውያን ማንን ይጠባበቁ ነበር?

ሀ- እነርሱ አዳኝ እንዲልክላቸው እግዚአብሔርን ይጠባበቁ ነበር።

- እግዚአብሔር ታጋሽ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎች ከኃጢአት መንገድ ተመልሰው የእርሱን መንገድ እስኪከተሉ ድረስ ይጠብቃል።

- እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን ሰዎች ከኃጢአት መንገድ ተመልሰው የእርሱን መንገድ እስኪከተሉ ድረስ ለ120 ዓመታት ጠበቃቸው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከኃጢአት መንገድ ተመልሰው የእርሱን መንገድ እስኪከተሉ ድረስ ለ200 ዓመታት ጠበቃቸው።

- ነገር ግን እስራኤላውያን ከኃጢአት መንገድ አልተመለሱም።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን የሚረሳ መሰላቸው?
- እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ረስቶአል?
- አልረሳም።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን እንደማይቀጣ መሰላቸው።
- እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው ሰዎችን ይቀጣል?
- አዎን።

- እግዚአብሔር በኖኅ ዘመን የነበሩትን ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት እንደ ቀጣ ሁሉ እስራኤላውያንንም በኃጢአታቸው ምክንያት ቀጥቷል።

- እግዚአብሔር ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች እንዴት ቀጣቸው?

- እግዚአብሔር አሦራውያን ልኮ ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶችን አሸንፈው ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው አደረገ።

# 2ኛ ነገሥት 17፡5-8

5- የአሦርም ንጉሥ አገሩን በሙሉ ወረረ፤ ወደ ሰማርያም ገሥግሦ ሦስት ዓመት ከበባት።

6- በሆሴዕ ዘመነ መንግሥት በዘጠነኛው ዓመት፣ የአሦር ንጉሥ ሰማርያን ያዘ፤ እስራኤላውያንንም በምርኮ ወደ አሦር አፈለሳቸው። እነዚህም በአላሔ፣ ጎዛን ውስጥ በአቦር ወንዝ አጠገብ እንዲሁም በሜዶን ከተሞች እንዲሰፍሩ አደረገ።

7- እንግዲህ እስራኤላውያን ይህ ሁሉ ሊደርስባቸው የቻለው፣ ከግብፅ ምድር ከፈርዖን አገዛዝ ከግብፅ ንጉሥ ያወጣቸውን አምላካቸውን እግዚአብሔርን ስለ በደሉት ነው፤ እንዲሁም ሌሎች አማልክትን በማምለክ፣

8- እግዚአብሔር ከፊታቸው አሳዶ ያወጣቸውን የአሕዛብን አማልክት፥ የእስራኤልም ነገሥታት ወደ ምድሪቱ ያገቡትን አጸያፊ ልማድ ስለ ተከተሉ ነበር።

- አሦራውያን ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች አሸንፈው ብዙዎቹንም ወደ አሦር በመውሰድ ባሪያ አድርጓቸው።

- አሦራውያን ከሌሎች አገሮች ሰዎችን አምጥተው ከቀሩት እስራኤላውያን ጋር በእስራኤል ምድር እንዲኖሩ አደረጉ።

- ከሌሎች አገሮች የመጡት ሰዎች ለቀረጿቸው ምስሎች የሚሰግዱ እንጂ በእግዚአብሔር የሚያምኑ አልነበሩም።

- እነዚህ ሰዎች በእስራኤል ምድር ከቀሩት እስራኤላውያን ጋር ተጋቡ ከዚያም አዲስ ዓይነት ዝርያዎች ተፈጠረ።

- እነዚህ አዲስ ዓይነት ዝርያዎች ሰማርያውያን ይባሉ ነበር።

- ሰማርያውያን በእግዚአብሔር መንገድ ሳይሆን በራሳቸው መንገድ እግዚአብሔርን አመለኩ።

- እግዚአብሔር ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች ከቀጣቸው በኋላ በይሁዳ ያሉትን ሁለቱን ነገዶች እንዴት ቀጣቸው?

- እግዚአብሔር ባቢሎናውያንን ልኮ በይሁዳ ያሉትን ሁለቱን ነገዶች አሸንፈው ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው በማድረግ ቀጣቸው።

2ኛ ነገሥት 25፡1-7

1- በይሁዳ ንጉሥ በሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት በዘጠነኛው ዓመት በዐሥረኛው ወር፣ ከወሩም በዐሥርኛው ቀን የባቢሎን ንጉሥ ናቡከድናጾር መላ ሰራዊቱን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ዘመተ፤ ከከተማዪቱ ቅጥር ውጭ ሰፈረ፤ ዙሪያውንም በሙሉ በዕርድ ከበባት።

2- ከተማዪቱም እስከ ሴዴቅያስ ዘመነ መንግሥት ዐሥራ አንደኛ ዓመት ድረስ እንዲሁ እንደ ተከበበች ቈየች።

3- በአራተኛው ወር በዘጠነኛው ቀን በከተማዪቱ ውስጥ የተከሠተው ራብ ጸንቶ ስለነበር ሕዝቡ የሚቀምሰውን አጣ።

4- ምንም እንኳ ባቢሎናውያን ከተማዪቱን እንደከበቧት ቢሆንም የከተማዪቱ ቅጥር ተጣሰ፤ ሰራዊቱም ሁሉ በንጉሡ አትክልት አጠገብ ባሉት በሁለቱ ቅጥሮች መካከል በሚገኘው በር አልፎ በሌሊት ሸሸ፤ ሸሽቱም ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ ነበር።

5- ይሁን እንጂ የባቢሎን ሰራዊት ንጉሡን ተከታትሎ በኢያሪኮ ሜዳ ላይ ደረሰበት። ወታደሮቹ ሁሉ ተለይተውት ተበታትነው ነበር።

6- እርሱም ተያዘ፤ በዚያን ጊዜ ሪብላ ወደ ነበረው ወደ ባቢሎን ንጉሥ አመጡት፤ ቅጣትም ተፈረደበት።

7- ሴዴቅያስ ዓይኑ እያየም የገዛ ልጆቹን ገደሉበት፤ ከዚያም ሁለት ዐይኖቹን በማውጣት በናስ ሰንሰለት አስረው ወደ ባቢሎን ወሰዱት።

- ባቢሎናውያን ሁለቱን የይሁዳ ነገዶች አሸንፈው ብዙዎቹን ወደ ባቢሎን ወስደው ባሪያዎች አደረጓቸው።

- ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ከተማ ደመሰሱ።

2ኛ ነገሥት 25፡9-12 & 21

9- የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ፣ ቤተ መንግሥቱንና በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ቤቶች ሁሉ አቃጠለ፤ እያንዳንዱንም ታላላቅ ሕንጻ ለእሳት ዳረገው።

10- በክብር ዘቡ አዛዥ የተመራው መላው የባቢሎን ሰራዊትም በኢየሩሳሌም ዙሪያ የነበረውን ቅጥር አፈረሰው።

11- የክብር ዘቡ አዛዥም በከተማዪቱ ቀርቶ የነበረውን፣ ከድቶም በዚያ የተገኘውን ሰው ሁሉ ወደ ባቢሎን ወሰደው።

12- ሆኖም አዛዡ ከአገሬው ሰዎች ምንም የሌላቸውን ድኾች ወይን እንዲተክሉ፣ ዕርሻም እንዲያርሱ እዚያው ተዋቸው።

21- ይሁዳም ከምድሩ በዚህ ሁኔታ ተማርኮ ሄደ።

- ባቢሎናውያን የኢየሩሳሌምን ከተማ የደመሰሱት እንዴት ነበር?

- ቤተ መቅደሱን በእሳት አቃጠሉ።

- የኢየሩሳሌምን ከተማ በሙሉ አቃጠሉ።

- በከተማዪቱ ዙሪያ ያለውን ቅጥር አፈረሱ።

- እግዚአብሔር ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶችና ሁለቱን የይሁዳ ነገዶች ከኃጢአት መንገድ ባለመመለሳቸው ምክንያት ቀጣቸው።

- ከብዙ ዓመታት በኋላ ባቢሎን ይኖሩ የነበሩት የይሁዳ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ።

- ወደ እግዚአብሔር ጮኹ ኃጢአታቸውን ለእርሱ ተናዘዙ ይቅርታም እንዲያደርግላቸው ለመኑት።

- እግዚአብሔር መሐሪ በመሆኑ ብዙዎቻቸው ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እንዲመለሱ ፈቀደላቸው።

- የይሁዳ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ በተመለሱ ጊዜ ምን አደረጉ?

- ቤተ መቅደሱን እንደገና ሰሩ።

- የኢየሩሳሌምን ከተማ እንደገና ሰሩ።
- በኢየሩሳሌም ከተማ ዙርያ ያለውን ቅጥር እንደገና ሰሩ።

- ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት የይሁዳ ሰዎች በአዲስ ስም ተጠሩ።

- ወደ ኢየሩሳሌም ለተመለሱት ለይሁዳ ሰዎች የተሰጠው አዲሱ ስም ምን የሚል ነበር?
- አይሁድ።

- ምንም እንኳ አይሁዶች እግዚአብሔርን ቢያመልኩም ለቀረጿቸውም ምስሎች መስገዳቸውን ቀጥለው ነበር።

- ስለዚህም እግዚአብሔር ተጨማሪ ሁለት ሕዝቦች ልኮ እንዲያሸንፏቸው አደረገ።

- እግዚአብሔር አይሁዶችን እንዲገዙ የላካቸው ሁለት ሕዝቦች እነማን ነበሩ?
- ግሪኮችና ሮማውያን

- በመጀመርያ እግዚአብሔር ግሪኮችን ልኮ አይሁድን እንዲያሸንፉ አደረገ።

- ግሪኮች አይሁድን ወግተው በማሸነፍ መሬታቸውን ያዙ።
- ግሪኮች የግሪክን ቋንቋ ለአይሁዳውያን አስተማሩ።

- ከግሪኮች በኋላ እግዚአብሔር ሮማውያንን ልኮ አይሁድን እንዲያሸንፉ አደረገ።

- ሮማውያን አይሁዶችን ወግተው በማሸነፍ መሬታቸውን ያዙ።

- ሮማውያን አይሁዶች ቀረጥ እንዲከፍሏቸው አደረጉ።

- ሮማውያን ብዙ አይሁዳውያንን ከእንጨት በተሠራ መስቀል ላይ ሰቀሏቸው።

- የሮማውያን ንጉሥ ቄሣር ይባል ነበር።
- ቄሣር በሮም ከተማ ይኖር ነበር።

- ሮማውያን ማንን ያመልኩ ነበር?
- ሮማውያን ብዙ ምስሎችን ያመልኩ ነበር።
- ሮማውያን ንጉሣቸው ቄሣርንም ያመልኩ ነበር።

- በዚያ ጊዜ በኢየሩሳሌም ውስጥ ሦስት የአይሁድ የአመራር ቡድኖች ነበሩ።

- እነርሱም ጸሐፊዎች ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ነበሩ።
- አንዳንዶቹ የአይሁድ መሪዎች ጸሐፊዎች ይባሉ ነበር።

- ጻፎች እነማን ነበሩ?

- የእግዚአብሔርን ቃል የሚጽፉ የአይሁድ መሪዎች ነበሩ።

- ከረጅም ዘመናት በፊት ዛሬ እንዳሉን ዓይነት መጽሐፎች አልነበሩም።

- ሰዎች አንድን ነገር መጻፍ በሚፈልጉበት ጊዜ ከጫፍና ጫፍ በሚጠቀለል ረጅም ወረቀት ላይ ይጽፉ ነበር።

- ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል የጻፈው ከጫፍና ጫፍ በሚጠቀለል ረጅም ወረቀት ላይ ነበር።

- ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ይፈልጉ ስለ ነበር በአዳዲስ መጻፊያ ወረቀቶች ላይ የእግዚአብሔርን ቃል መጻፍ ያስፈልግ ነበር።

- ቀኑን ሙሉ ጻፎች በአሮጌዎቹ ውረቀቶች ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል ወደ አዲሶቹ ወረቀቶች ይገለብጡ ነበር።

- ጻፎች ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚጽፉ ይኮሩ ነበር።

- ጻፎች ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚጽፉ ቃሉን አውቀነዋል ብለው ያምኑ ነበር።

- የእግዚአብሔርን ቃል መጻፍ ብቻውን ቃሉን እንድታውቁት ያደርጋል?
- አያደርግም።

- ጻፎች ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ይጽፉ ስለ ነበር ኃጢአት እንደሌለባቸው አድርገው ይቆጥሩ ነበር።

- የእግዚአብሔርን ቃል መጻፍ ብቻውን ያለ ኃጢአት እንድትሆኑ ያደርጋል?
- አያደርግም።

- አብዛኞዎቹ ጻፎች በእግዚአብሔር አያምኑም ነበር።

- ሌሎቹ የአይሁድ መሪዎች ደግሞ ፈሪሳውያን ይባሉ ነበር።

- ፈሪሳውያን እነማን ነበሩ?

- ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ የአይሁድ መሪዎች ነበሩ።

- ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ሕግ ደግሞ ለአይሁዶች ያስተምሩ ነበር።

- በተጨማሪም ፈሪሳውያን የራሳቸውን ሕግ ደንግገው ለአይአሁዶች ያስተምሩ ነበር።

- ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ሕጎች ሁሉ እንደሚታዘዙ ያምኑ ነበር።

- የእግዚአብሔርን ሕጎች በሙሉ መታዘዝ የሚችል አለ?
- የለም።

- ፈሪሳውያን ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚያስተምሩ በጣም ይኮሩ ነበር።

- ፈሪሳውያን ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚያስተምሩ ቃሉን እንደ ተረዱ ያምኑ ነበር።

- የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ብቻ ቃሉን እንድትረዱት ያደርጋል?
- አያደርግም።

- ፈሪሳውያን ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምሩ ስለ ነበር ራሳቸውን ኃጢአት እንደሌለባቸው አድርገው ይቆጥሩ ነበር።

- የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ብቻ ያለኃጢአት እንድትሆኑ ያደርጋል?
- አያደርግም።

- አብዛኛዎቹ ፈርሳውያን በእግዚአብሔር አያምኑም ነበር።

- ሌሎቹ የአይሁድ መሪዎች ደግሞ ሰዱቃውያን ይባሉ ነበር።

- ሰዱቃውያን እነማን ነበሩ?
- ሰዱቃውያን ሀብታሞችና የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች የሆኑ አይሁዶች ነበሩ።

- ሰዱቃውያን ሀብታሞችና የቤተ መቅደሱ ጠባቂዎች በመሆናቸው በጣም ይኮሩ ነበር።

- ሰዱቃውያን እጅግ ብዙ ገንዘብ ስለ ነበራቸው ኃጢአት የሌለባቸው አድርገው ራሳቸውን ይቆጥሩ ነበር።

- ባለ ብዙ ገንዘብ መሆን ብቻውን ያለ ኃጢአት እንድትሆኑ ያደርጋል?
- አያደርግም።

- አብዛኛዎቹ ሰዱቃውያን በእግዚአብሔር አያምኑም ነበር።

- በእነዚህ ጊዜያት አይሁዶች ምኩራብ የሚባሉትን ቤቶች ሠሩ።

- ምኩራቦች ምንድን ናቸው?

- ምኩራቦች አይሁዶች የሙሴን መጽሐፎች ለማንበብና ለመወያየት የሚሰበሰቡባቸው ቤቶች ነበሩ።

- አይሁዶች በሁሉም ከተሞቻቸው ውስጥ ምኩራቦችን ሠርተው ነበር።

- በሳምንቱ የመጨረሻ ቀን አይሁዶች ወደ ምኩራቦቻቸው ይሄዳሉ ከዚያም ከሙሴ መጽሐፎች የሚነበብላቸውን ያደምጣሉ።

- ብዙ ጊዜ ሰዎች የሙሴን መጽሐፎች ያብራራሉ።

- ይሁን እንጂ ሰዎቹ በእግዚአብሔር ስለማያምኑ በሙሴ መጽሐፎች ላይ የሚሰጡት ገለጻ ትክክል አልነበረም።

- በዚያን ጊዜ፥ አብዛኞቹ አይሁዶች በእግዚአብሔር አያምኑም ነበር።

- በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር የሚያምኑ አይሁዶች ነበሩ?
- አዎን።